# አዎ ! የኤርትራው ፎቶ ይናገራል ።

## ከጋዜጠኛ ደምስ በለጠ

ከቀናት በፊት በአንድ ቃለ-መጠይቅ ላይ የአንድ ተዋጊ ድርጅት መሪ እዚህ አሜሪካ ተቀምጦ እንዴት ነው በሪሞት ኮንትሮል ጦር ሊመራ የሚችለው ብዬ ተችቼ ነበር ። ዛሬ ከወሬ አልፎ በአመነበት የትግል ስልት ወደተግባር ተሸጋግሮ ብርሃኑ ነጋ ወደ አስመራ ማቅናቱን አድንቂያለሁ ።

ከብርሃኑ ነጋ ጉዞ ሁለት የሻእቢያ ትያትር ሴናሪዎ እጠብቃለሁ ። አንደኛው ብርሃኑ ነጋን ሻእቢያ ወታደራዊ ዩኒፎርም ያለብሰዋል ። ከዚያም ሰራዊቱን ወደ ሃሬና ማሰልጠኛ ጣቢያ ወርዶ እንዲጎበኙ ያደርገዋል ። በዚያም ሻእቢያ ትልቅ የፕሮፓጋንዳ ስራ ይሰራበታል ።

ቀደም ሲል በአንድ ፅሁፌ ላይ እንደገለፅኩት የአርበኞች ግንባርና የግንቦት 7 ውህደት ተዋጊዎች ቁጥር ዛሬ ግፋ ቢል ከ150 አይበልጥም ። ይህም ቁጥር ሰራዊት አለኝ ብሎ አድምቆ ለመናገር ሙሉ መተማመኛ አይሆንም ። ወይም የምንሰማውን አይነት የጦርነት ፕሮፓጋንዳ ግዳይ ሊያስጥል የሚችል ሃይልም አይደለም። ያም ሆኖ ታዲያ ፤ ለፕሮፓጋንዳው ስራና ሰልፍ ድምቀት ሲባል የድምህት ወታደሮች የሰልፉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል ። ይህን አይነት የሻእቢያ ፊንታ ከጀመሪያው ጉዞዬ ጀምሮ በተደጋጋሚ አይቻለሁና ።

ሁለተኛው ሴናሪዎ ደግሞ ከብርሃኑ ነጋ መምጣት ጋር የአርበኞች ግንቦት 7 ውህደት ከሌሎች ድርጅቶች በተለይም ከድምህት ጋር አሊያንስ ፈጠረ ተብሎ አዋጅ ይነገራል ፤ መግለጫዎች ይወጣሉ ፤ ከበሮ ይደለቃል ። ለዚህ ትያትር ማዳመቂያ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በምርኮ ከተያዙ የደቡብ ተወላጆች በሆኑ ሰዎች ሻእቢያ ያቋቋማቸው ሁለት ወይም ግፋ ቢል ሶስት አባላት ያላቸው የደቡብና የቤንሻንጉል ድርጅቶችም ተሳታፊ ናቸው ተብለው የአሊያንሱ ማጫፈሪያ ይሆናሉ ።

እነዚህን ሁለት ሴናሪዎዎች አብረን እንጠብቅ ።

አምስተኛ ወሩን ያስቆጠረው የአዲሱ ውህደት መግለጫ ደሞ ትንሽ አደናግሮኛል ። እንዲህ ይላል ። ያሰመርኩበትን ደግሞ አጢኑልኝ ።

"አርበኞች ግንቦት 7 አመራሩን ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን እና ትግሉ በሚጠይቀው ቦታ እንዲገኙ የሚያደርግ መሆኑ ሲገልጽ ቆይቷል። አሁን ትግሉ በደረሰበት ደረጃ የአመራሩ በትግሉ ሜዳ ውስጥ መገኘት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት <u>በዚህም መሠረት የንቅናቄው ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ወደ ትግል ሜዳ ወርዷል።ሊቀመንበሩን ጨምሮ አመራሩን ወደ ትግሉ ሜዳ አንቀሳቅሷል።</u> ...በአሁኑ ሰዓት የንቅናቄው አመራር በተሟላ ሁኔታ በትግሉ ሜዳ ውስጥ እንዲገኝ ማድረግ ተችሏል።" ይላል ።

የሄዱት ሁለት ሰዎች ናቸው ። አመራሩን ወደ ትግሉ ሜዳ አንቀሳቅሷል ማለት ምን ማለት ይሆን ?

የአመራሩን ወደአስመራ መውረድ በተመለከተ የሚቀርቡ ዜናዎች ከፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ውጪ ወጥነትና ግልፅነት ሊኖራቸው ይገባል እላለሁ ።

አሁን ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ላምራ።




ይህን ፎቶ ከቀኝ ወደግራ ይመልከቱ ። የኢትዮጵያን ባንዲራ በእጁ የያዘው ሰው የለበሰው ወታደራዊ ዩኒፎርም ፤ የሻእቢያ ወታደራዊ ሰርቪስ ዩኒፎርም ነው ።

ከሱ ቀጥለው ሶስቱ የቆሙትና አንዱ የተቀመጠው የለበሱት ቅጠልያ ሬንጀር

ዩኒፎርም የአርበኞች ግንባር ዩኒፎርም ነው ። ከዛ ቀጥለው በካኪ ዩኒፎርም ያሉት ስድስቱ ደግሞ የድምህትን ዩኖፎርም ነው የለበሱት ።

በአርበኞች ግንቦት ሰባት መሪዎች አቀባበል ላይ የሻእቢያው ወታደር ምን አገባው ?  በሻእቢያ አሰራር እንደተለመደው በፎቶ የሚታዩትን ሰዎች እንቅስቃሴና አንደበት ለመቆጣጠር የተመደበ  ነው ።

የሚቀጥለውን  ፎቶ ደግሞ ተመልከቱ ።



ከብርሃኑ ነጋና ከነአምን ዘለቀ ኋላ በሰማያዊ ቲ ሸርትና በጥቁር ጃኬት መግቢያው በር ላይ ያለው ኑርጀባ አሰፋ የአርበኞች ግንባር ሰው ነው ። ቅጠልያ ኮፍያ ና አመድማ ዥጉርጉር ልብስ የለበሰውና ብርሃኑ ነጋንና ነአምን ዘለቀን ከድምህትና ከአርበኞች አባላት ጋር እያስተዋወቀ ያለው ደግሞ የሻእቢያ መደበኛ ሰራዊት የበታች ሹማምንት ዩኒፎርም ነው የለበሰው ። ይህ የሻእቢያ የበታች ሹም በምን ስልጣን ነው "ለአርበኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ"  መሪ ለብርሃኑ ነጋ ፤ የራሱን ድርጅት ሰራዊት አባላት የሚያስተዋውቀው ?

"የመኻል አገር ሰው ካከባበርከውና የአቀባበል ስነስርአት ካደረክለት ብሎም ካሞካሸኸው ከፍከፍ ካደረከው ከዚያ በላይ ጠልቆ የሚፈልገውና የሚጠይቀው የለም" ሲሉ ሻእቢያዎች ይመጻደቃሉ ።

ከኢሕአግና ከግንቦት 7 ውህደት በኋላ ብርሃኑ ነጋ የድርጅቱ መሪ ሲባል የአርበኞች መሪ የነበረው መአዛው ጌጡ የሰራዊቱ አዛዥ ተብሎ ተመድቦ እንደነበር ሰምተናል ። ወታደሮቹ የሱ ታዛዦች ከሆኑ በእዙ ስር ያሉትን ማስተዋወቅ የመአዛው ስራ መሆን አልነበረበትም?

በነዚህ የፎቶ አቀባበል ስነስራት ላይ መአዛው ጌጡ የለም ። ወዴት ሄደ ? እንደጦር አዛዥነቱ በሰሜን ኢትዮጵያ በወልቃይት ፤ በጠገዴና ፤ በአርማጮሆ ፤ ግንቦት 7 የከፈተው ውጊያ ላይ እያዋጋ ነው እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። መአዛው ጌጡ በውጊያ ላይ ከተሳተፈ ወደ አስራ ሁለት አመታት አልፎታል ።

ምክንያቱም እንዲህ ነው ። የዛሬ አስራ ሁለት አመታት ገደማ መአዛው በኤንትሬ መኪና  ተሳፍሮ ሲጓዝ መኪናው ተገልብጦ ከፍተኛ የወገብ አደጋ የደረሰበት ሰው ነው ። ከአመት በፊትም እንዲሁ ሌላ የመኪና አደጋ ደርሶበት እግሩ ተሰብሮ ያለ ሰው ነው ። ምናልባት በሃሬና ማሰልጠኛ ጣቢያ ከላይ የጠቀስኩትን የሻእቢያ ሴናሪዎ ትያትር በኮለኔል ፍፁም አቀናባሪነት እያዘጋጀ ሊሆን ይችላል ።

ቀድሞ ወደ አስመራ ተጉዘው የነበሩ ሰዎችን ልምድ መመልከት ወይም መረዳት እስካልቻሉ ድረስ እነ ብርሃኑ ነጋም ተመሳሳይ ስህተት እንዲፈፅሙ ይደረጋሉ ፤ ማኖም ይነካሉ ። አንዴ ሻእቢያ ማኖ ካስነካቸው ደግሞ ሁሌ እያስጎነበሰ ቅጣት ምት ይመታባቸዋል ።

ከላይ ፎቶዎቹ ላይ እንደሚታየው የመጣው ሁሉ የነሱ መስሎአቸው መሞኘት የለባቸውም ። በተለይ በተዋጊዎቹ ስም የሚገናኟቸውን ሰዎች ማንነትና በግንባሩ ያላቸውን ስልጣን ሊያውቁና በመዋቅር ላይ የተመሰረቱ ግንኙነቶች ብቻ ማድረግ ይገባቸዋል ። ይህ የድርጅት ነጻነታቸውን ለመጠበቅ ሊያግዛቸው ይችላል ። ከልምድ እንደተረዳሁት እንቁላሎችህን ሁሉ ባንድ ቅርጫት ውስጥ አድርገህ ለሻእቢያ ማስረከብ ከፍተኛ አደጋ አለው ።

ዛሬ ሻእብያ የተዋጊዎቹ ተወካዮች ብሎ የሚያቀርባቸውን ሰዎች ነገ በሌሎች ይተካቸዋል ። ስለዚህ ብርሃኑ ነጋም ሆነ ነአምን ዘለቀ ከጀርባቸው ምን እየተሰራ እንደሆነ ገና ሊረዱት አይችሉም ። ዩኒፎርም ለብሶ የመጣ ሁሉ የነሱ መስሎ ታይቷቸው ከሆነ ተሳስተዋል ።  ከጊዜ ጋር ግን ይገነዘቡታል ብየ እገምታለሁ ።  ያኔ ታዲያ ባቡሩ ሄዷል ።

በዚህ አጋጣሚ ማሳሰብ የምፈልገው ለኢትዮጵያ ነፃነት እንታገላለን የሚል ድርጅት መሪዎች ወደአስመራ ሲገቡ ፤ ከባለስልጣናቱ ጋር በሚያደርጉት ውይይት የኢትዮጵያውያንን መብት ማስቀደም ልዩ ተግባራቸውና ባህላቸው ሊያደርጉ ይገባል ። በኤርትራ እንደነኮለኔል ታደሰ ሙሉነህ አይነቱን በግፍ የታሰሩ ወገኖችን ጉዳይ አንስቶ ስለነፃነታቸው መከራከር የኢትዮጵያዊነት መብት መለኪያ እሴት ማሳያ ስለሚሆን ሊያስቡበት ይገባል እላለሁ ። ይህን የመሰሉ ጉዳዮችን ከግብ ማድረስ መሪዎች ነን በሚሉ ሰዎች ላይ የዜጎችን እምነትና ተስፋ ያለመልማል።

ከአውሮፓም ፤ ከአውስትራሊያም ፤ ከሰሜን አሜሪካም ሄደው የነበሩት ሁሉ ተስፋ ሰንቀው ሄደው በየጊዜው እንዲሁ እየተሸወዱ ነው የተመለሱት ። ይህን ሁሉ ለመረዳት ታዲያ ኮለኔል ፍፁምንና ሻእቢያዊ ተልእኮውን ከዚያም አልፎ የግል ፍላጎቱን እንዴት እንዴት በተዋጊዎቹ ላይ እንደሚያስፈፅም ጠንቅቆ መረዳት የግድ ይላል ።

ሰሞነኛዎቹን ሴናሪዎዎች ደሞ አብረን እንጠብቅ ።

7/21/2015 እ.ኤ.አ.
ላስ ቬጋስ ኒቫዳ ።